# ይሄይስ ተኣምኖ በእግዚኣብሔር

ከይሄይስ አእምሮ

- በቀለም የተመለከቱት ፊደላት የሚጠብቁ ናቸው፡፡

እንደምን ሰነበታችሁልኝ፡፡ ባገራችን አንድ አባባል አለ፤«ከብቶች እንኳን በየፊናቸው ዱር ውለው ማታ ሲገናኙ ‘እምቡዋ’ በመባባል ሠላምታ ይለዋወጣሉ፡፡» የሚል - በሌላም በኩል «እንደከብት ዝም ብለህ አትቀላቀል » የሚለውን ቢፃዊ ግሳጼም ሳንዘነጋ፡፡ በ’ርግጥም ነገርን በሠላምታ መጀመር ጥሩ ነው - አሁንም «ከሺህ ሠላምታ አንድ ሜታ!» ወይም «ሦስት ጊዜ ሠላምታ አንዱ ለነገር ነው!» የሚባሉትን ጸረ-ሠላም(ታ) ኃይሎች ማለቴ አባባሎች ሳንረሣ፡፡ እናም ሠላምታየ በያላችሁበት ይድረሳችሁ፡፡

ግዕዛዊ መንደርደሪያየ «በእግዚኣብሔር መታመን ይሻላል» የሚል ነው፡፡ መገስገሻየንና መድረሻየን የሚያውቀው ግን እርሱው ራሱ ነው - ከእምነት ዉጪ በዓይን የማይታየውና በዕጅ የማይዳሰሰው ፈጣሪ፡፡ «አነሳስቶ ላስጀመረኝ አንድዬ ምሥጋን ይግባውና . . .» ቀልቤ በመራኝ የሙንጨሬ ፈረሴን ልኮልኩል፤ እናንተም እንዳፈተታችሁ፤ አንድም ከኔው ጋር ቆዩ፤ አንድም . . . ቃል አጠረኝ - ብቻ ከኔው ጋር ቆዩ፡፡(አያ ጅቦ፣ ምግብ ቀርቦ የአያ አንበሣን መምጣትና ‘ቡራኬ’ ለሚጠባበቁ ሌሎች እንስሳት ምን አለ መሰላችሁ - ‘እንበላው እንደሁ እንብላው፣ እንተወውም እንደሁ እንብላው’ እንተወው ለማለት አንጀቱ አልቻለለትም፡፡)

የኢትዮጵያን ጠላቶች ቁጭ ብዬም ሆነ ተኝቼ ሳስባቸው በዓይነትም በመጠንም በመፍትሔ ማጠጥም ግራ አጋቢ የመሆናቸው ጉዳይ እንደማኛውም ጤናማ ኢትዮጵያዊ ያስጨንቀኛል፡፡ እናም ብዙውን ጊዜ ‘ጨርቅህን ጣልና ይለይልህ’ ይለኛል - ጨርቅን መጣል መፍትሔ የሚያመጣና የዋዛ ነገርም ይመስል፡፡ የዘመኑ ክፋትና የእግዜሩ ገደብ የለሽ የሚመስል ትዕግሥተኝነት ደግሞ የባሰውን አንጎል ያደርጋሉ፡፡ ዱሮ’ኮ ብድር በምድር ነበር - አሁን ግን ፈጣሪ ሥንቱን አፍርጨ ልቸርስ ብሎ ተስፋ ቆርጦ ይመስላል ነገር ዓለሙን ትቶታል፡፡ ዳሩ አይጥና ድመት፣ ውሻና ሌባ፣ ገዳይና ሟች፣ፖሊስና ቀማኛ . . . ታሪካዊ ቁርሿቸውን ያለድርድር ወደጎን በመተው በሥልታዊ ጠብን የመርሳት ዘዴ ባንድ ማዕድ በሚቆርሱበት ዘመን የፍርድ መዘግየት ምን ያስገርማል? ሥንትና ሥንት ጀግኖችና ብርቅዬ ምሁራንን በጠራራ ፀሐይ ያስፈጀች አገር አንድ ምሥኪን ዜጋ አማኑኤል ሆስፒታልን ቢቀላቀል ደንታ እንደማይሰጣት ይልቁናስ ቢዘገይም አደብ ገዝቶ መጪውን የፈጣሪ ፍርድ በጉጉት መጠበቅ እንደሚሻል ጓደኞቼ ሲመክሩኝ ትንሽና ለጊዜው  ቀለል ይልልኛል፡፡ ለነገሩ ሞትና ዕብደትም ባቅማቸው እዬኮሩ ሥንቶቸን በደጅ ጥናት እያንከራተቱ መሰላችሁ - እዚህ ኢትዮጵያ ውስጥ? ብሂላዊ ተረቱ «ካልነገዱ ወይ ካላበዱ የልብ አይገኝም»ና «ሞት ርስት ነው» ስለሚል ብናብድና ብንሞት የልባችን የሚደርስ፣ ርስተ ጉልትም የምናገኝ እየመሰላቸው ሳይሆን አይቀርም ሁለቱም ከወያኔ ጋር ተመሣጥረው እየዶለቱብን ናቸው፡፡ ሌላውስ ይሁን እንዳሻው - አሁን ሞት እንኳን ይንጠባረርብን? እነፕሮ. አሥራትን፣ እነአሰፋ ማሩን፣ እነፋንታሁን ወርቁን ፣እነመባጽዮን ጃተኒን፣ እነፀጋዬ ደብተራውንና በበርካታ ሺዎች የሚቆጠሩ ሌሎች ለሀገር ነጻነትና ለፍትሕ ተሟጋች ወገኖቻችንን . . . ወያኔን ተመስሎ በጉያችን ገብቶ አልመነተፈብንም? ታዲያ አሁን ምን ታየውና ብዙዎቻችንን በቁም እዬገደለ ልብስ የለበሰ ሬሳችን ብቻ በየመንገዱና በየአደባባዩ እንዲንጠራወዝ ፈቀደ? ለምን አይለይልንም? «ተኖረና ተሞተ» እንደተባለው ወጉ አይቀርምና «በኢትዮጵያ መሬት ላይ ኖረዋል» ተብለን “እላይ” ስንሄድ ልንታማ አይደል? አቅጣጫን ባለማወቂ ነው ‘እላይ ’ን “እላይ” ያልኩት፡፡ አዲስ አበባን ብታዩዋት በአሁኑ ወቅት ከጥቂት ባለጊዜዎች በስተቀር አብዛኛው ነዋሪ በቁሙ ሞቷል ማለት ይቻላል፤ በእዉነት ደንዝዘናል፡፡

ከተጨባጩ ነባራዊ ሁኔታ አኳያ ማንም እንደሚረዳው ትልቁ የኢትዮጵያ የወቅቱ ጠላት ወያኔ ለመሆኑ ዋቢ መንቀስ ሳያስፈልገን ብዙዎቻችን የምንተማመንበት ዓቢይ ጉዳይ ይመስለኛል፡፡ ከዚያ በመለስ ለተፈጠረው  ችግር ሁሉ ግን የኛም ሚና እንዳለበት ማመን ይኖርብናል፡፡ (በጣም የተቸገርኩባትን ይቺን ዐረፍተ ነገር ያጢኑልኝ!) እኛ አነማን ነን?

አንድ ወይም ጥቂት ሰዎች ከመሬት ተነስተው ሀገርን ያህል ግዙፍ ነገር እንዴት ሊያጠፉ እንደሚቻላቸው በተመስጦ ለጥቂት ቅጽበት እናስብ። በብሂላችን «ቂጣም ከሆነ ይጠፋል፤ ሽልም ከሆነ ይገፋል» ይባላል - የውሸትንና የእውነትን እያደር መክሰም ወይም መግነን ለማጠየቅ። ከዚህ ተጠየቃዊ አመክንዮ ተነስተን የወያኔን አነሳስና የ«ዕድገት» ደረጃ ስንታዘብ አነሰም አደገም የሁላችን አስተዋፅዖ ሳይታከልበት በ60ዎቹ አጋማሽ አካባቢ ከአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ትምህርታቸውን «ለሕዝብ ጥቅም»ሲሉ አቋርጠው ደደቢት (ስም ይቀድሞ ለነገር ይላሉ አበው!) በረሃ የሸፈቱቱ የዚያን ጊዜዎቹ እምቦቀቅላዎች የዛሬዎቹ ወጣት ሽማግሎች ይህን ሁሉ «የሀገር ዕድገት»ና ብልግና ማለቴ «ብልጽግና» ያመጡ ነበር ወይ? ብለን ብንጠይቅ አጥጋቢ መልስ ለመስጠት የሚያስችል የሞራል ብቃትና የመንፈስ ጥንካሬ የሚኖረን አይመስለኝም።

«እግዜር ሲቆጣ ሽመል አይቆርጥም፤ ያደርጋል እንጂ ነገር እንዳይጥም» ይባላል። ወያኔ በብዙ መስዋዕትነትም ቢሆን መንገዱ ቀኝ በቀኝ የሆነለትና በለስ ቀንቶት ሊያውም ሳያስበው አጋጣሚዎች የፈጠሩለትን ክፍተት ተጠቅሞ የምኒልክን ቤተ መንግሥት ለአንዴና እንደስካሁኑ አካሄዱ ከሆነ ደግሞ ምናልባትም ለመጨረሻ ጊዜ ተቆጣጥሮ የሚገኘው በርሱ ጥንካሬ ሳይሆን በኢትዮጵያ «ሕዝቦች» ለጨካኝ አገዛዞች አመቺነት ነው - ካለበት የተጋባበት ይባል የለም? «ሕዝቦች» የሚለው ቃል እንዴት ይቀፋል? ብሂሉም የሚያጸናው «የተበይዎች አለመስማማት ለበዮች ያመቻል»ሲል ነው። እኛ አንግዲህ እንዲህ ነን፤ ሚዛን በማይደፋ ትንሽ ነገር ላይ ስንረባረብና ለመነካከስ ስንራኮት ለጉድ ነው፤ በጣት የሚቆጠሩ ተንኮለኞችና ሸረኞች ለሚሸርቡብን ገመድ በኅብረት ሆ ብለን አንገታችንን ስንሰጥ፣ መንጋ የቀን ጅብ በመሃላችን ገብቶ በ«ማን አባት ገደል ገባ!» የልጆች ጨዋታ አስተኔ ትብታቡ አፍዝዞ ርስ በርሳችን ሲያፋጀን ፣ በወንዝና በቀዬ ዓይነ ርግብ ከልሎ ራሱ ያሻውን እየዘረፈና በዕጅ አዙር እያዘረፈ አንጡራ ሀብታችንን ሲያሸሽና እያስማማ ሲሸጥ ፣ ፍጹም ማስተዋል በተሳናቸው ግብረ በሎቹና ኅሊናቢስ ተባባሪ ዘውገኞቹ ሚሊዮኖችን ሲረጋግጠን . . . ግን የሚሰማን አንመስልም። ምን ነክቶን ይሆን? የትውልድ ዕርግማን ይሆን? እንዳንስማማ በመካከላችን ሟርትና ደንቃራ ተጥሎብንስ ይሆን? በጥቂት ሽዎች የሚቆጠሩ በጎሣና በቤተሰብ ተቋጥረው በላያችን ላይ ዳንኪራ ሲመቱ፣ እኛ ደግሞ በሌላ ወገን ባመቻቹልን ጥንታዊ የከፋፍለህ ግዛ ሥልት እየተናቆርን ተራ በተራ ግን በ'ርግጠኝነት ሁላችንም እየሞትን እነሱ በመቃብራችን ላይ ጮቤ ሲረግጡ በትዝብት ብቻ የምንመለከታቸው በእውኑ ምን ነክቶን ይሆን? እስኪ ጥቂት የቢቸግር መላምቶችን ልጠቁም፤

ከምታዘበው ማኅበራዊ ሕይወት ተነስቼ ጥቂት ነገር እንድናገር እንደፈቀዳችሁልኝ ልቁጠርና ወደዚያው በቀጥታ ልሂድ። ተማረ የተባለው የኅብረተሰብ ክፍል በፍርሀት ተሸብቦና በኢኮኖሚያዊ የጎልውና ሥጋት 'ተጠርንፎ' አንድም በአቶ መለስ አንደበት ዘወትር እንደምትወሳው ሰጎን አንገቱን ደፍቶ በ"እስኪያልፍ ያለፋል" ተረት ተጀቡኖ ተደብቋል፤ አንድም የትሚናውን ተሰድዶ ጉልበቱን ወይም ዕውቀቱን በመሸጥ ሕይወቱን በ«እህህ» ይገፋል፤ አንድም በተስፋ መቁረጥ ስሜት ለአልባሌ ሱሶችና መጥፎ ልማዶች ተጋልጦ ከደስታ የራቀ ዘግናኝ ኑሮውን ባጭር ለመቅጨት ታጥቆ ተነስቷል፤ አንድም ኅሊናውን ደብቆ ወይም ሸጦ በአድርባይነት ለወያኔ ፍርፋሪ በመረታት በሙስና በበሰበሰውና ከጫፍ እስከግርጌ በገማው ቢሮክራሲያዊ የዕዝ ጠገግ ሥር አንጀት ላይ ጠብ ለማይል የዕለት ጉርስ በተዋራጅነት ተመሽጓል - (መንገዱ ካልተዘጋበትም የሙስናው ፍሬ ተቋዳሽ መሆኑ አያጠራጥርም)፤ አንድም ከለየለት ደም መጣጭ ስግብግብ ነጋዴ ጋር ተመስጎ በ'ሀገር ሲወረር አብረህ ውረር' የዓሣሞችና የባሕርይ ዘመዶቻቸው የጅቦች ፈሊጥ ቀን የጎደለበትን ሕዝብ ሥጋና አጥንት በመጋጥ ታሪካዊ የንቅዘት ተልዕኮውን በመወጣት ላይ ይገኛል፤ የ«መሪጌታ ይሄይስ» አንድምታ በዚህ መልክ ይቀጥላል - መነሻ እንጂ መድረሻ በሌለው ሁናቴ። እዚህ ላይ መታሰብ ያለበት አንድ ዋና ጉዳይ ግን ምንም እንኳን በተለያዩ አጣብቂኞች ውስጥ ቢገኝም ሀገርን ከወያኔ የግፍና የጭቆና መሪር አገዛዝ ነጻ ለማውጣት የተማረው የኅብረተሰብ ክፍል ምን ማድረግ ይጠበቅበታል? የሚለው ነው።

ወጣቱን የተመለከትን እንደሆነ «የትኛው ወጣት?» ብለን እስከመጠየቅ ወደሚያደርስ የችግር አዘቅት ውስጥ እየገባን ያለን ይመስለኛል። ወጣቱ ከፊት ለፊቱ በሞዴልነት የሚያየው በሁሉም የሥራና የትምህርት መስኮች ስኬታማነት አንቱ የተባለ ኢትዮጵያዊ ለማግኘት በገረረው የቀትር ፀሐይ እንደ ፈላስፋው ዲዮጋን ፋኖስ ይዘን ብንፈልግ አንድ ስንኳ የማግኘታችን ጉዳይ አጠያያቂ ከሆነ ሰንብቷል። የኋለኞቹም ርቀዋል፤ የወደፊቶቹም ላሁኑ ችግራችን ባይጠቅሙንም ስለመምጣታቸው እርግጠኞች መሆን አንችልም። የዘመኑ ፈሊጥ በ«የትም ፍጪው. . .» ባንድ ቀን

አዳር የስኬት ማማ ላይ ወጥቶ ፌጢጥ ማለትና እንደደራሽ ጎርፍ ድንገት በሚገኝ ሀብትና ዝና ሕዝብ ላይ መንጎማለል  እንጂ እንደ ጥንት እንደጧቱ በልፋትና በጊዜ ሂደት የሚገኝ የትምህርት ደረጃም ሆነ የሀብት ክብረት «ፋራ»ና «ባላገር» የሚያሰኝ ሆኗል፡፡ ይህንና ሌላውን ወያኔያዊ የጎሣና የዘር መድሎ እያዩ የሚያድጉ ወጣቶች የትኛዋን ሀገር እንደሚረከቡ ዕድሜ ከሰጠን ገና ወደፊት የምናየው ይሆናል፡፡ በዚያ ላይ በትምህርት ገዳይ ፖሊሲ የተቀፈቀፉ የማንኛውም ዓይነት የትምህርት ደረጃ ተመራቂዎች ከዕውቀቱ ብፌ በዛ አድርገው እንዳያነሱ የወያኔው አገር አጥፊ የትምህርት ሥርዓት ጨካኝ የማይምነት ካባውን ስለጣለባቸው ብዙዎቹ ለማለት በሚያስችል ሁኔታ ብቃታቸው አስተማማኝ አይደለም፡፡ ምንም እንኳን የቋንቋ ዕውቀት ብቻውን ሌሎች ጽንሰ ሃሳባዊ ግንዛቤዎችንና ክሂላዊ ክንዋኔዎችን ለመለካት ባያስችለንም፤”I doesn’t knew there name.”ና “ They knows we.” የሚሉ የቢኤ ዲግሪ ተመራቂዎች ኢትዮጵያ ውስጥ በብዛት ብታገኙ - ከዕውነተኛ መረጃ ተነስቼ ነው የምነግራችሁ - እንዳትገረሙ፡፡ የወያኔው የትምህርት ሥርዓት ከዚህም በላይ ጉድ ሠርቶናል ጎበዝ! እናም «ያልዘሩትን መሰብሰብ» አይቻልምና በወጣቱም ረገድ ያለን ተስፋ በዜሮና በአንድ መካከል እንዳይሆን ፈጣሪ ይጠብቀን ብሎ መጸለይ ነው፡፡ በትምህርቱ ጥራት ላይ ያለው ችግር ሳያንስ ከ«ጳጳስ» እስከአናጉንስጢስ ከጠ/ሚኒስትር እስከ ተራው ዜጋ ድረስ ያመነኸኩታል ከሚባለው የወቅቱ ወረርሽኝ ጫት ጀምሮ በልዩ ልዩ ሱሶች አብዛኛው ወጣት የተጠመደ በመሆኑ ሱሱን የሚያስታግስበትን ዘዴ ከማለም ባለፈ ሀገርን ነጻ ለማውጣት እንኳንስ እንደዱሮው የኢሕአፓ ዘመን ራያ ጎመጅና ወልቃይት ጠገዴ ሊዘምት ይቅርና እንጦጦ ላይ ሆኖ በቤተ መንግሥት አቅጣጫ ድንጋይ ቢወረውር ጥቂት የማይባለው ወጣት ልቡ ውልቅ ብላ ነው የምትወጣ - ሊያውም ለዚህም ወኔው ከተገኘ፡፡ ወያኔና ሻዕቢያ እኮ የመቶ ብቻ ሣይሆን የብዙ መቶዎች ዓመታት የቤት ሥራ ነው የሰጡን፡፡ የክፋታቸው ውቅያኖስ እንዴት ጥልቅ ቢሆን ይሆን ከ30 ዓመታት በላይ ቀድተው የማይጨርሱት?

የእኔ ቢጤው ወደሚመደብበት ምንም ወዳልተማረው ወይም በመጠኑና በልምድ ወይም በጥራዝ ነጠቅ ዕውቀት ግማሽ ብስል ግማሽ ጥሬ ወደሆነው ሕዝበ አዳም ስንመጣ ብዙም ተስፋ ሰጪ ነገር አናገኝም፡፡ በ«ሆድ ይፍጀው»ና «ተከድኖ ይብሰል» ካላለፍነው በስተቀር ነገረ ሥራችን ከማሳዘን አልፎ ያስለቅሳል፡፡ ብሶቴን በአንድ እውነተኛ ምሳሌ አስደግፌ ላስረዳ፡፡

« . . . ባልና ሚስቱ አንድ ልጅ ብቻ ነው ያላቸው፡፡ እግዚሃሩ መርቆላቸው ዩኒቨርስቲ የሚያስገባ ነጥብ አገኘና ተመርቆ ሥራ ያዘላቸው፡፡ ግን ምን ዋጋ አለው፤ ሥራ በያዘ በጥቂት ወራት ውስጥ አበደና እንጦጦ ማርያም ጠበል ገብቶ ለሰባት ዓመታት በሠንሰለት ታሥሮ ሊጠበል ተገደደ - እናቱ እያስታመሙት፡፡ በላዩ ላይ የሠፈረው ፀላኤ ሠናያት(ሰይጣን) በልጁ አንደበት ሲለፈልፍ የልክፍቱ መንስዔ የልጁ አባት የወንድም ሚስት ማለትም የአጎቱ ባለቤት እንዳስደገመችበት ታወቀ፡፡ ምክንያት - የሴትዮዋ በርካታ ልጆች ምንም ደረጃ ላይ ሳይደርሱ ይሄ ልጅ ስለተሳካለት በቅናት መንፈስ ተነሳስታ ‘እንደዋለችበት’ ተደረሰበት፡፡ በሰባተኛው ዓመት ግን ልጁ በእናትየው የእምነት ጽናት ከበሽታው ተፈውሶ በቀድሞውም ባይሆን በሌላ መሥሪያ ቤት ተቀጠረ፡፡ አሁን በልጁ ቤተሰብ ውስጥ ሃማኖት ወርዶ፤ ሠላምም ሰፍኖ በመልካም ሁኔታ ላይ ይገኛሉ፡፡ . . .»

እኛ እንዲህ ነን፡፡ ከዚህ በላይ ያስቀመጥኩት  እውነተኛ ታሪክ ለዛሬው መጣጥፌ መነሻ የሆነኝ ልብን ሰባሪ ታሪክ ነው፡፡ ይህንና ከሕዝባችን ቁጥር እምብዝም የማይተናነሱ መሰል ታሪኮችን ስንታዘብ ለዚህ ዓይነቱ ፌር የለቀቀ ዕኩይ ምግባራችን ወያኔ ሲያነስን ነው ብንል ሊፈርድብን የሚቃጣ መኖር የለበትም፡፡ ፈጣሪ ደገኛን ሕዝብ ሊክስ ሲፈልግ ምን እንደሚያደርግ የሚገነዘብ ሰው ተቃራኒውን ማሰብ እንደማይሳነው ግልጽ ነው፡፡ « አንቺም ጨካኝ ነበርሽ ጨካኝ አዘዘብሽ ፤እንደገና ዳቦ እሳት ነደደብሽ» የምንለው ወደን አይደለም፡፡ በሀገር ቤትም ይሁን በከተማ፤በመሥሪያ ቤትም ይሁን በሠፈር፤ በጓደኛሞች መካከልም ይሁን በሌሎች የጽዋና የዕድር ማኅበር አባላት፤ በቤተሰብ ውስጥም ይሁን በረጃቶች(ራቅ ያሉ ዘመድ አዝማዶች)እና በጎረቤቶች መካከል፤ በካህናትም ይሁን በመነኮሳት አካባቢ፤ በገዳምም ይሁን በካቴድራል፤ በጳጳሳትም ይሁን በኤጲስ ቆጶሳት፤ ምን አታከታችሁ በሁሉም ዘንድ የሚታየው በድግምትና በትብታብ የመጠላለፍ አባዜና ከሃይማኖት የወጣ ጎጂ ልማድ እጅግ ያስደነግጣችኋል፡፡ መጠላለፉና መነቃቀፉ የፖለቲከኞቻችን ብቻ ሳይሆን የአብዛኛው ማኅበረሰባችን ባህል የሆነ ይመስላል፤ እውነትን ተናግሮ የመሸበት ማደር እየተቻለ ጉድን ታቅፎ በ«እህህ» መኖር ይብቃን ብለን ሃቁን መናገር ከደፈርን እንዲያውም ፖለቲከኞቹ የኅብረተሰቡን ሥር የሰደደ የመናቆርና አንዱ ላንዱ ወጥመድ የመዘርጋት

ጎታች ባህል በሥልት አዳብረውና አዘምነው ነው እንዲህ የሚናቸፉት ቢባል አሳምሮ ያስኬዳል:: በዝርዝር እንየው ከተባለ ከራስ ገጠመኝ  በመነሳት ጭምር ብዙ ስንክሳር መጻፍ ይቻላል:: በአንደርብ ቤቱ የሚታመሰውን፤ በጥንቆላ ሳቢያ ሕይወቱና ትዳሩ የፈረሰውን(እነታምራት ገለታን እዚህ ላይ ያስታውሷል)፤ በመተት ምክንያት ኑሮው የተቃወሰውን፤ በሥራ ሥር በጣሽ- በመጽሐፍ ገላጭ- በሥኒ ተመልካች- በአውሊያና ከራማ- ቦረንቲቻና በጠጠር ወርዋሪ- በሞራ ተመልካችና በኮከብ ቆጣሪ- በዛር ፈረስና በቆሌ ባዲገዝ- በደብተራና በቃልቻ- በጋንኤል ጎታችና በድቤ መች- በሰው ደም የጭዳ መስዋዕትና በመሳሰለው አጋንንታዊ የድግምትና የአስማት ቱማታ የተኮደኮደውን ወገናችንን ብናስብ በሃይማኖት የለሽ የሃይማኖት መሪዎቻችን በእጅጉ እናፍራለን:: ቄሱንና የደብር አለቃውን ጨምሮ እስከተራው ምዕመን ድረስ ሌሊት በቃለ እግዚኣብሔር «ይዌድስዋ መላእክት. . .» ሲል አድሮ ተሲያትና አመሻሽ ላይ በየአዶከብሬው ቤት «መጀን በናንተ፤ በቸር ግቡ፤ ፈረሳችሁን አታሰቀዪ. . . አዳል ሞቲ እሳት  ቆርጣሚው - ዋስ አንጋች በረኸኛው- አንበሦ ሸቶ ትራሱ- ጠቋር ቡሌ በፍም ተራማጁ . . .» እያለና እያስባለ ለሁለት ጌቶች የሚገዛውን የገበቴ ውኃ እንታዘባለን:: ይህን ስል ፈሪሃ እግዚአብሔር አድሮባቸው የፈጣሪን መንገድ በመከተል ለነፍሳቸው ያደሩትንና እንደፈሪሳውያንና ሰዱቃውያን ለታይታ ሳይሆን «በሥውር ለሚያደርጉት ተጋድሎ» ዋጋቸውን በግልጽ ባደባባይ እንደሚያገኙት መልካም ሰዎች የሚመስሉትን ወገኖቻችንን እንዳልሆነ ይታወቅልኝ፤ የዱሮ ፊሊፕስ «ጥሩ ዕቃ ማስታወቂያ አያስፈልገውም» ይል ነበር የኋለኛው ተለዋጭ ማስታወቂያ «ካለማስታወቂያ መነገድ ቆንጆ ልጃገረድን በጨለማ ውስጥ እንደመጥቀስ ነው!» ብሎ ባያፈርሰው:: እኔ የምለው የማይመለከተው ይደሰት፤ ወደዚያ ወጥመድ እንዳይገባም ይጠንቀቅ - ለምን ቢባል «መጠንቀቅ ያለበት ቆሞ ያለ የሚመስለው ነውና!» «ምንትስ ያለበት ዝላይ አይችልም.» እንደሚባል ከምጠቃቅሳቸው መልካም ያልሆኑ ጠባያት በአንዱ ወይ በሌላው እንከን ያለብን ወገኖች ከመነቃቀፋችን በፊት ቆም ብለን ውስጣችንን ብንዳብስ ባንጠቀም እንኳን አንጎዳም::  ገመናችንን ለመቃኘት ድፍረት እንዲሰጠን አምላክን ተንበርክኬ እለምናለሁ፤ በፈጣሪ የምታምኑ የጸሎት ኃይላችንን እናስተባብር - ካሜን ብቻ አይደለም ከልብ ካለመጸለይም ይቀራል::

የሽፍንፍንና የጥግንግን ጉዞ የትም ስላላደረሰን እያንዳንዳችን በኅሊና መስተዋት ተራዳኢነት ጉድፋችንን እያየን ማበስ ካልቻልን በእስካሁኑ ዝግመታዊ ጉዞ ፍትሃት የትም መድረስ እንደማንችል መገንዘብ ይኖርብናል:: ቁስል በተሸፈነ ቁጥር - ስሜት ጎፍናኝ ቃል ባለመጠቀም ስገልጸው ይብስበታል እንጂ ወደ ድኅነት አይሄድም - በፍጹም::  እናም ባህላችን ተነካ፤ የ«ቅዱሳን» አባቶቻችን ስም ጎደፈ ማለት የምንችለው በቅድሚያ ሀገር ሲኖረንና ተተኪ ትውልድ ማፍራት ስንችል ብቻ መሆኑን ተረድተን ከዚህ በላይ በደምሳሳው ከጠቃቀስኳቸው ዘርፈ ብዙ ማኅበራዊና ፖለቲካዊ አረንቋዎች ባፋጣኝ ለመውጣት የየአቅማችንን ሳንለግም ከአንጀታችን እንጣር:: ባለንበት እንርገጥ ብለን ከመረጥንም መብታችን ነው - ግን በማንኛውም ዘርፍ ሌባና አጭበርባሪ በፖለቲካው እኒያን የፈረደባቸው «ዴሞክራሲ፤ ነጻነት፤ፍትሕ፤እኩልነት፤ ወንድማማችነት...» የመሳሰሉ ቃላተ ኦሪት ዘዴሞክራሲያዊ ዕብለት እየዘመረ እደስከዛሬ ሁሉ ያላግጥብናል፤ በሃይማኖቱም ከተኩላና ቀበሮ ቆዳ በተሠራ  ካባና ልብሰ ተክህኖ የተጀቦኑ ውስተዘዎች እኒያን የፈረደባቸው «. . .አትግደል -አታመንዝር- በሀሰት አትመሥክር - የጓደኛህን ሀብት ንብረቱንም ሆነ ሚስቱን ... አትመኝ. . .» የሚሉ ወርቃማ ቃላተ ወንጌል ዘብሉይ ወዘሐዲስ በ«የምንላችሁን እንጂ የምናደርገውን አታድርጉ» አፍዝ አደንግዝ ልፋፌ ጽድቃቸው የአባሪ ደብዳቤ ሸኚነት መጋታቸውን ይቀጥላሉ::

እንዲህ ነበርን፤ አሁንም እንዲህ ነን:: ለቀጣፊና ለአጭበርባሪ የተመቸን፤ ለወንበዴና ለማጅራት መቺ የሰጠ ጫንቃ ያለን፣ ራሳችን ለራሳችን በፈጠርናት ትንንሽ ዓለማት ውስጥ በር ዘግተን የምንንጫጫና የምናንጫጫ፤ «እኛ ጋር ካልሆንክ የነሱ ነህ» በሚል የሲብስቴ ሕገ ኦሪት ታምሰን የምናምስ፣በጋራ ትግልና ጥረት የዘመናት የችግርና የጭቆና ቀምበር ዘባተሎኣችንን አውልቀን እንዳንጥል  በባሕሩ ይሁን በገደሉ ወይም በሁለቱም «የተደገመብን» 'የበረከተ መርገም' ምንዱባን ነን - እኛ ኢትዮጵያውያን::

ራሳችንን እንጠይቅ - ከዓለም በስደተኞች ብዛት ስንተኞች ነን? ለምንስ እንዲህ በገፍና በየመንግሥታዊ ሥርዓቶቻችን እንሰደዳለን? ከአሳዳጆቻችንና ከእኛ ከተሳዳጆቹ በምልዓትም ይሁን በብልሃት ማን ይበልጣል? ለምን በሁሉም ነገር ወደታች ወረድን? በመልክ፣ በዘር፣ በብሔራዊ የዜግነት ማንነት፣ በጋርዮሻዊ ግፍንና በደልን የመጋፈጥና የመረገጥ ታሪክ፣ በሥነ ልቦና፣ በኢኮኖሚና በመሳሰለው ሁሉ ተቀራራቢ ሆነን ሳለን በመካከላችን ምን ነፋስ ገብቶ ነው እንዲህ ለጠላቶቻችን በሚያመች አኳኋን ዝምታንና ጸጥ ለጥ ባይነትን የመረጥነው? «ባለቤት ካልጮኸ ጎረቤት አይደርስም» እንዲሉ እኛ የወያኔ አገዛዝ የተመቸን ያህል የሆዳችንን በሆዳችን ይዘን የዝምታ እረጭታ ወይም ሰመመን ውስጥ ከገባን ማን ስለመብታችን ሊታገልልን ይችላል? . .

እነዚህ ጥያቄዎች የተሰነዘሩት ለድረ ገጽ ያለው ቀረቤታ ከኢትዮጵያ ሕዝብ ውስጥ 0.4 በመቶው ይሆናል ተብሎ ለሚገመተውና ይህችን መጣጥፍ ደግሞ እንደዕድል ሊያነባት ለሚችል በጥቂት አሥሮች ለሚገመት የሕዝብ ክፍል መሆኑን አውቃለሁ - ግን የሰማ ላልሰማ ያዳርስ፤ፈጣሪም ልመናና ጸሎታችንን ሰምቶ አስተዋይ ልቦናና ጥበብ የተላበሰ፣ ከምንዳክርበት ሰው ሠራሽ ድጥ እኛ ው እያገዘነው ፈጥኖ የሚያወጣን እውነተኛ ሙሴ ይላክልን፡፡

በመሠረቱ ነገር እየተወላገደብኝ በአራምባና ቆቦ እዚህ ደረስኩ እንጂ አነሳሴ - በየትኛው ሚዲያ እንደማገኘው ባላውቅም - ከፍ ሲል በገለጽኳቸው የባዕድ አምልኮዎችና ከትክክለኛው የፈጣሪ ትዕዛዛት የወጡ ሰውን የመጉጃም ሆነ የመጥቀሚያ መንገዶች ገብቶ አሣሩን እየበላ ለሚገኘ ው ወገን የበኩሌን የመፍትሔ ሃሳብ ለመወርወር ነበር፡፡ እንደ እውነቱ ከሆነ ይሄ የባዕድ አምልኮ ነገር በሀገራችን እጅግ በጣም አሳሳቢ ደረጃ ላይ ደርሶኣል፡፡ ጫፍ ላይ ከሚገኘው የመንግሥትም ሆነ የሃይማኖትና የግል ኢንቬስትመንት ተቋም ባለሥልጣንና ኃላፊ ጀምሮ እስከታችኛው ምንዝር ድረስ ዱሮ በአዩኝ አላዩኝ አሁን አሁን ደግሞ በልበ ድፍንነት በገሃድ በዬጠንቋዩና በዬደብተራው ቤት የማይጎናበስ የለም ማለት ይቻላል- ለነፍስና ለሀገር ለወገን መሥራት እንደወንጀል መቆጠሩም ከዚህ ኅሊናን ስቶ ለሀብትና ለሥልጣን ከሚደረግ ሩጫ የተነሣ ነው፡፡ የተራውን የሆቴልና ባልባለቁ ሕጻናት . . . የሚተከሉትን የውኃና የኮረንቲ ወፍጮዎችን ታሪክማ ተውት፡፡ እኔ የምለው የ«ታላላቆቹ»ን ነው፡፡ ሀሰቴን ብሆን እኔው ልኮነንበት ኘ ከንፈራችሁን አትንከሱልኝ፡፡ «ሁሉን ቢናገሩት ሆድ ባዶ ይቀራል» እንዲሉ ሆኖብኝ እንጂ የሥንትና ሥንት «ስመ ጥር» ዜጎቻችን ድጓና ዝማሬ መዋሲት ተገልጦ ቢነበብ ሥንት ሀብትና ንዋይ በአስማታዊ የ«ዶፒንግ» መዘዝ ምክንያት ወደ መንግሥት ካዝና በገባ ነበር - ደግነቱ መንግሥትም ራሱ ከ«ዶፒንግ» ጣጣ የአንበሣ ድርሻውን ስለማያጣ መንግሥት እስኪገኝ አንዱ ታማኝ ጋ ባደራ ይቀመጥ እንደሆነ እንጂ፡፡

ችግራችን እንደዚህ የተወሳሰበ ከሆነ ዘንድ ምን እናድርግ? ዝም ብለን «የዓለምን ፍጻሜ» እንጠብቅ ወይንስ የተሻለ አማራጭ ይኖረናል? በጎቻቸውን ሜዳ ላይ በትነው ቁማር የማይጫወቱና በተኩላና ሺላ የማያስጨርሱ የፖለቲካና የሃይማኖት መሪዎችን እንዴት እናግኝ? «በአርኣያ ሥላሴ የተፈጠረ የሰው ዘር ሁሉ በእግዚአብሔር ዘንድ አንድ ነው» ብሎ በተግባራዊ ምሳሌነት ራሱን አስቀምጦ ደገኛዪቱን የጽድቅ መንገድ የሚያሳይ የሃይማት አባት የምናገኘው መቼ ነው? በብዛቱ ብቻ ሳይሆን በአእምሮኣዊ ብስለቱ የመጠቀ፤ ለማንም አጭበርባሪና ቁጭበሉ የወሮበላ ቡድን የግፍ አገዛዝ የማይመች፤ በአጋር ወንድሙና በንጹሕ ጎረቤቱ ሳይሆን በሀገሩ የውጭም ሆነ የውስጥ ጠላት ላይ ከሌሎች ወገኖቹ ጋር በኅብረት በመዝመት ልኩን የሚያሳይ የነቃና በዘመናዊ አስተሳሰብ የዳበረ ኅብረተሰብ እንዴት እንገንባ? ገንዘብን የሚያመልኩ መዥገር የመንግሥት ባለሥልጣናትና የጥቅም ሼሪኮቻቸው ዓይን አውጣ ነጋዴዎች መቼ ነው ኮብራዊ የእባብ ኁድፈያቸውን የሚያቆሙልንና እፎይታ የምናገኘው? በየሰዉ ሀገር የተበተነው የሠለጠነ የሰው ኃይላችንና ሀገር ሊያለማ የሚችል በስደት ያፈሩት ቅርሳቸው ወደ ሀገር ገብቶ ኢትዮጵያችንን መቼ ነው ከበለጻጉ አገሮች ተርታ ማሠለፍ የምንችለው? መቼ ነው በራሳችንና በሀገራችን የምንኮራው? መቼ ነው አንዳንድ የዋህ ወገኖቻችን ፈረንጅ የሆኑ እየመሰላቸው ፈረንጅም ኢትዮጵያዊም ሳይመስሉ እንደልዩ ማስፈራሪያ ፍጡር መቆጠራቸው የሚያበቃው? (እዚህ ላይ ፀጉርን የፈረንጅ ለማስመሰል ማቅለምን- አለባበስን- አነጋገርን - አረማመድን. . .ያስቡዋል) መቼ ነው በማንነታችን ሳይቀር አምርረን እንድንዘምትበት እያስገደደን ያለውን ሀገራዊ የዘመናት ጨቅቅት በተውሶ ሳይሆን በገዛ እንዶዳችን ሞዥርቀን ከላያችን የምናስወግደው? . . የእስካሁኑን አንድዬ ከጠበቀኝ አሁን ሳትሰለቹኝ ልሰናበት፤ እግዚአብሔር በቃችሁ ብሎ ኢትዮጲያንና እኛን ሕዝቡዋን ከገባንበት የመከራ አዘቅትና ተደጋጋሚ አዙሪት ባፋጣኝ እንዲያወጣን ቤሃይማኖታችን ዘወትር እንጸልይ፡፡ የመልዕክቴ ድምፀት ከተለመደው የማለባበስ ይትበሃል በጥቂቱ ያፈነገጠ ስለመሰለኝ ድረ ገጾቻችን ይህን ጽሑፍ ለማስተናገድ ሳይቸገሩ አይቀሩም የሚል ግምት አለኝ፤ ብርታቱን ይስጣቸው ከማለት ውጭ ምን እላለሁ? ይሁን ያለው ይሆናል - እኔ ግን ለጊዜው በጣም በትንሹ ‘እፎይ’ ብዬ ተገላገልኩ፡፡ እንደተለመደው ገምቢ አስተያየታችሁን በከፍተኛ ጉጉት እጠብቃለሁ፡፡ አስጀምሮ ላስጨረሰኝ አምላክ አኮቴት ይገባዋል፡፡

yiheyisaemro@gmail.com